# ምርጫ ወይስ ስህተትን ለመድገም/ለማሰደገም ሩጫ?

(ከመላኩ ይስማው)

እስከዛሬ ድረስ ብዙ ምርጫዎች ተካሂደዋል። በአፄውም፣ በኮሎኔሉም፣ በብፃዩም አገዛዝ የተለያየ ምክንያት እየተሰጠንና እየተለመን ወይም እየተገደድን መርጠናል። መቼም ሌላ ስም የለውም "ምርጫ" ነው የሚባለው።

ዛሬ ደግሞ የአለፈው "ምርጫ' ፋይል ሳይዘጋና ተከትሎ የተከሰተውም መዘዝ በአግባቡ እልባት ሳያገኝ እንዲንመርጥ "እየተጋበዝን" ነው። የምርጫዎቹ ታሪክ እንደሚያስረዳውና የነበሩትም እንደሚያውቁት ሁሉም ምርጫዎች "እንዲታምኑን ጨፈኑ" ከማለት ያለፈ ትርጉም ያልሰጡና ምንም ዓይነት መሰረታዊ ሕዝባዊ ጠቀሜታ ያላስገኙ ናቸው። መጭውም ምርጫ በምኑም በምኑም ከአለፉት የተለየ እንደማይሆን ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አይጠይቅም። እንዳለፉት ምርጫዎች ሁሉ፣ አማራጮች ኖረውን ከመካከላቸው የምንፈልገውን የምንመርጥበት ሳይሆን ተጋዳይ/ገዳይ "መንግስታችን" አስቦና ተቀርቁሮ፣ ተጨንቆና ተጠቦ፣ ራሱ ፈቅዶ ከሚያቀርብልን አማራጮች መሀል ያሸነፉ መሆናቸውን የሚነግረንን ወንበርተኞች ተቀብለን የምናጸድቅበት ተውኔት ነው። በአጭር ቋንቋ ተመርጦ ለሚቀርበልን በውድም በግድም ይሁንታ የምንሰጥበት፣ ባንሰጥም እንደሰጠን የምንነገርበት ቧልት ነው። ከዚህ ውጭ ነው ሊሉን የሚሹ ካሉ፣ ከቀኝ ሆነ ከግራ፣ በእጅጉ የናቁን፣ እነሱ በበሉ እኛ ቁንጣን እንዲይዘን የሚጠብቁ፣ በህዝባዊ አገራዊ መብታችንና ሉዓላዊነታችን ላይ የሚሳለቁ ዘመናይ ስራ ፈላጊ የፖለቲካ በረንዳ አዳሪዎች እና የስርዓቱ ፍርፋሪ ለቃሚዎች ብቻ ናቸው። ከፍ ሲል እንደጠቆምኩት፣ ያለፉትን ምርጫዎች ባህርይ መነሻ በማድረግ መጭውም ምርጫ ለህዝቡ ምንም ጥቅም የማያስገኝ ቧልት ነው ብሎ መደምደም በእጅጉ ትክክል ነው።

የይስሙላ ሳይሆን የእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ዓላማ መራጩ ህዝብ ውሳኔውንና ፍላጎቱን በሰላማዊ መንገድ መግለጽ እንዲችል ማብቃትና ይህንኑ ውሳኔና መብቱን ማረጋገጥ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ምርጫ ራሳቸውን ለምርጫ የሚያቀርቡ ተፎካካሪ ሃይሎች አጀንዳቸውን ለህዝቡ በማስተዋወቅ የህዝቡን አመኔታ ለማግኘት ይጥራሉ። ህዝቡም ከመካከላቸው ይጥቅመኛል ያለውን ይመርጣል። በምርጫው አብላጫ ድምጽ ያገኘው ወገን ደግሞ ሃላፊነቱን ተረክቦ በምርጫዎች መካከል ባለው ጊዜ የተሰጠውን ተልዕኮ ያከናውናል። ይህ በምንም ይሁን በምን አይሸራረፍም። ይህ ባልሆነበት፣ የህዝብ ድምጽ በማይከበርበት፣ ባለነፍጥ የስልጣን ልጓም በመያዝ እንዳሻው በሚፏልልበትና የንጹሃንን ደም በሚያፈስበት፣ በተቃዋሚነት መደራጀት ወንጀል በሚደረግበት አገር ምርጫ ብሎ ነገር ፍጹም ቀልድ ነው። ከቀልድም ቀልድ፣ እጅግ በጣም አሳዛኝ ቀልድ!

የአገራችን የምርጫ ጉዳይም ከዚህ የተለየ አይደለም። ባለነፍጡ የትላንት በረኸኛው፣ የዛሬው የከተማ ማጅራት መቺ ቡድን በህዝብ ለመቀለድ ቀን እየቆጠረ የሚሰራው አስፀያፊና ህዝብን በመናቅ ላይ የተመሰረተ ርካሽ ተውኔት ነው። ባይሆንማ ኖሮ የትላንቱ የህዝብ ድምጽ ተረግጦ ባለበት፣ ህዝቡ ለመብቱ በመቆሙ በአረመኔዎች እብሪተኛ ውሳኔ የፈሰሰው ደሙ ባልደረቀበትና ቁስሉ ባልሻረበት፣ የመለስ አገዛዝ ፈቅዶ ከቀረቡለት የወቅቱ አማራጮቹ መካከል የፈቀዳቸው <u>ወኪሎቹም</u> የወከላቸውን ህዝብ ድምጽ ለማሰከበር በመነሳታቸው ብቻ ወንጀለኞች

መደረጋቸው ባልታረመበት ሁኔታ፣ ለሌላ ተመሳሳይ ቧልት ባልተጋበዘ ነበር። የህዝብ ወገን ነን ሲሉን የባጁትም ፍፁም ከሃዲ ሆነው ከህዝቡ ደመኞች ጋር ሲያሽቃብጡ ባልተመለከትን ነበር። ከዚህ ሂደት ለማትረፍ ክፉኛ የቋመጡትና ፀረ-ህዝቡ መንግስት፣ አሳዳሪ ጌቶቹና ታዛዥ ሎሌዎቹ የተቻለውን ያህል ሊያስማምሩት ቢሞክሩም መጪው ምርጫ ለብዙሃኑ የአገራችን ህዝብ የሚፈይደው አንዳችም ነገር ለም። በግልጽ አባባል ለማስቀመጥ ምርጨ ተብዬው ቧልት ወያኔ/ኢሕአዴግ እና በዙሪያው የተኮለኮሉ የህዝቡን ትግል የካዱና ያስመቱ እምነት በላዎች እንዳሻቸው እንዲሆኑና እንዲያደርጉ ስምምነታችንን እንድንገልጽላቸው የሚሰጡን ዕድል ነው።

ነገረ-ዓለሙ እንዲህ ሆኖ ሳለ ነው እንግዲህ ወደዚህ አጸያፊ ጨዋታ እንድንገባ የምንታደመው። በጣም የሚገርመው ደግሞ ይህ ይካሄዳል የሚባለው የዘንድሮው ምርጫ ከአለፉት ምርጫዎች ሁሉ በባሰ ሁኔታ መግቢያውም መውጫውም ጥርቅምቅም ብሎ የተቸነከረ መሆኑ ነው። ለዚህም ጥቂት ማብራሪያዎች መስጠት ይቻላል።

በመጀመሪያ ደረጃ የምርጫው ቅድመ-ዝግጅት ሁለንተናዊ ባህርያት ከአለፉት ምርጫዎች ሁሉ በበለጠ ሁኔታ ኢሕአዴግ አሸነፍኩ ብሎ ሊያጭበረብር በሚያስችለው መልክ የተጠናቀቀ መሆኑ ነው። አማቂው አገዛዝ በአለፈው ምርጫ ወግ አሳመርኩ ብሎ ሲቀናጣ ተዘናግቶና ለማስመሰል አስቦ የጀመረው “አደገኛ” ጨዋታ ያመጣበትን መዘዝ በሚገባ አጢኖ የዚያን ዓይነት ”ቅብጠት” ላለመድገም ሲሰራበት ቆይቷል። ይህ እንደሚሆን ደግሞ ድርጅቱ የምርጫውን ሂደትና ውጤት በገመገመበት ወቅት የደረሰበትን ድምዳሜ በገለጸበት ጊዜ የነገረን ጉዳይ ነው። በወቅቱ ኢሕአዴግ እንደ ኢሕአዴግ በግንባር ደረጃና በአባል ድርጅቶች ደረጃ፣ በተለይም በህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ [(ህወሓት) ህዝባዊ አብዮት ለትግራይ ነፃነት] ደረጃ ግምገማ ማካሄዱ የሚታወስ ነው። እነሱም ቢሆን የደበቁን ጉዳይ አልነበረም።

“እስካሁን ድረስ ባካሄድነው ትግል የትምክህት አመለካከትን የቀየርን መስሎን ነበር። አሁን ግን ስርዓትን እንጂ አመለካከትን ያልቀየርን መሆናችንን ተገንዝበናል። የትምክህት አመለካከት ገና ያልተሰበረ መሆኑን አጢነናል። ስለዚህም ይህንን አመለካከት ለመስበር እንቀሳቀሳለን።” ነበር ያሉን። ቃል በበቃል ባስቀምጥነው መልዕከታቸው ይህንን ነው ያሉን - ገዢዎቻችን። የትምክህት አመለካከት ማለት ምን ማለት ነው? የቱ ነው የትምክህት አመለካከት? ህዝብ የመሰለውን መምረጡ?! ኢሕአዴግን አለመምረጡ?! መምረጥ ትችላለህ ተብዬ ከመረጥኩ ድምጼ ይከበር ማለቱ?! ይህ ሁሉ ለኢሕአዴግ ትምህክት ነው። ይህም እንደማይደገም ነግሮናል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ኢሕአዴግ ያልሆነ ነገር እንዳይኖር ለማድረግ፣ ቢያንስ ቢያንስ እጅግ አብላጫው ወገን የኢሕአዴግ አባል ወይም አነብዳጅ እንዲሆን ሲሰራበት ቆይቷል።

ድርጅቱ ይህን ተግባሩን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በጥልቀት ሲያከናውን የቆዬ ቢሆንም በተለይ በትግራይና በአማራ ክፍል በስፋት ሲተገብረው ቆይቷል። በዚሁም መሰረት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ትምህርት ሲጨርሱ ስራ እንደማያገኙ በመደለልና ተጽዕኖ በማድረግ፣ የመንግስት ሰራተኞችና ሌላው

የህብረተሰቡ ክፍልም በዕድገት፣ በስራ ዓለም በመቆየት፣ በገንዘብና በማዳበሪያ ወይም ምርጥ ዘር ብድር፣ በግብርናና እንደልብ ለመንቀሳቀስ በመቻል፣ በእርሻ መሬትና በከተማ ቦታ ምሪት፣ ወዘተረፈ መሰል ጉዳዮች በማስፈራራትና በማግለል የድርጅቱ አባል እንዲሆኑ ሲሰራበት ባጅቷል። ሌላው ቀርቶ የዛሬ 20 ዓመት አሸንፌዋለሁ እያለ የሚያቅራራበት እና ችግር በገጠመው ቁጥር ግን ከመቃብር ተነስቶ እየተተናኮለኝ ነው በሚል አባባል የሚኮንነውን የኢሰፓ አባላትን እንኳ ሳይቀር ያልተወበት ጉዳይ ነው።

እነዚህን ትላንት ምንም ዓይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፉ አግዷቸው የቆዩትን በረባ ባልረባ በአመራሩ ደረጃና በደናቁርት ካድሬዎቹ አፍ ደርግ-ኢሰፓ እያለ ሲያብጠለጥላቸውና መግቢያ መውጫ ሲያሳጣቸው የኖሩትንም ሰዎች ሳይቀር የድርጅቱ አባል እንዲሆኑ በማስገደድ ጭምር ዘምቶበት መቆየቱን ስናጤን ድርጅቱ ምን ያህል ተጠቦ እንዳለና እንዳመረረ መረዳት እንችላለን። ይህ የቀቢፆ ተስፋ ተግባር የኢሰፓ መንግስት ባለቀ ሰዓት፣ ራሱን በራሱ ጠልፎ ለመጣል ሁኔታዎችን አደላድሎ ካበቃ በሁዋላ፣ ያንንም ያንንም አግበስብሶ አዲስ ፓርቲ ለማዋቀር በመወሰን ዶ/ር ዓለሙ አበበን "ሱሪህን በአንገትህ..." ዓይነት መመሪያ ሰጥቶ ከነበረበት ሁኔታ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል ነው።

(ደርግ ራሱን ጠልፎ ጣለ ማለቴ ይሰመርበት። የአጋጣሚ ወይም ለማለት ያህል የተባለ አባባል አይደለም። ጉዳዩ ለውይይት መከፈት ያለበት ቢሆንም አሁን አልገባበትም። በዚህ ዙሪያ ብዙ የውጭ ፀሐፊዎችና የመለሰ የፕሮፓጋንዳ ክፍል ብዙ እውነትነት የሌለው ታሪክ የፈበረኩበት ስለሆነ መታረም ወይም መመታት አለበት። ወደፊት ይመጣበታልና በይደር ትቼ ወደ አሁን ጉዳይ ልመለስ።)

በሁለተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚገባው ታላቅ ጉዳይ ደግሞ አሁንም ቢሆን የምርጫው ህግጋት፣ የምርጫው አፈፃፀምና አስፈጻሚው ሃይል በዋናነት የኢሕአዴግ የሆኑበትና በቁንጮ ካድሬዎቹ የቅርብ ክትትል የሚደረግባቸው መሆናቸው ነው።

በመሰረቱ እንኳንስ ከ70 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የሚኖርባት አገር መፃኢ ዕድል ለመወሰን የሚያስችል በትረ-መንግስት የሚጨበጥበት፣ ብዙ ዓይነት የተለያዩ የፖለቲካ አጀንዳዎች ያነገቡ ሃይሎች የሚሳተፉበትና ፍፁም ተራኳች ሆኑ አመለካከቶች የሚንሸራሸሩበት እንዲህ ዓይነት ታላቅ አገራዊ ስራ ቀርቶ የአንድ አነስተኛ ዕድር የስራ ተግባር የሚመሩ ጥቂት ሰዎች መምረጥ እንኳ ቢሆን ቀላል አይደለም። የተወሰኑ መስፈርቶች ሊበጁለትና መቆጣጠሪያ መንገዶችም ሊመቻቹለት ይገባል። እንዲህ ዓይነት ተግባር የሚያከናውኑት አካላት ተአማኒነት ደግሞ በግራ-ቀኙ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ መሆን አለበት። እንዲህ እንዲሆን ደግሞ አካላቱ እንኳንስ ለአንድ የፖለቲካ ሃይል ያደሉና በዚያው የተሾሙ ታማኝ መሳሪያዎች ሊሆኑ ቀርቶ በዚህ የሚጠረጠሩ እንኳን ሊሆኑ አይጠበቅም። ይህ ሊሆን በፍፁም አይገባም። ይህ ከሆነ ደግሞ ምርጫው ከዝግጅቱ ጀምሮ የተጨመላለቀ የሚሆን ብቻ ሳይሆን ሳይጀመር ያለቀ ሆኖ ነው የሚያርፈው። በእንዲህ ዓይነት የምርጫ ተውኔት የሚሳተፉ ሃሀይሎች ደግሞ የሕዝብን፣ የአገርን መብት ሊያስጠብቁ የሚነሱ ሳይሆኑ ሕዝባዊ አገራዊ ጥቅምን በራሳቸው ጠባብ ጥቅም የተኩ ፀረ-ሕዝብ ስብስቦች እና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ወገኖች ብቻ ናቸው ሊሆኑ የሚችሉት። በደረጃ፣ በመጠንና በዓይነት ቢለያዩም መሰረታዊ ዓላማቸው ይኸው

ነው የሚሆነው። እነዚህን ወገኖች ደግሞ የሕዝብን ጥቅምና መብት ተፃረው የቆሙ ወይ-ባይ የቀን ጅቦች ናቸው ከማለት የበለጠ ሊገልፃቸው የሚችል አባባል አላገኘሁላቸውም። ሌላ ምንም ቢሆኑም፣ ቢባዙም፣ ቢካፈሉም፣ መነባነበ ተውኔታቸውን ምንም ያህል ምን ቢያሳምሩትና ቢያጠጥሩት፣ ዓይነ-ህሊናቸውን ጋርደውና ራሳቸውን "አጃጅለው" የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ነን ባይ አጎብዳጆች የፈለጉትን ይበሉ፣ የአገሪቱ ተጨባጭ ፖለቲካዊ ሁኔታ የሚያሳየን ሃቅ ምኑም ምኑም በአስከፊ ዕመቃ ስር ተደፍጥጦ ያለ መሆኑን ነው። የፖለቲካ ስልጣኑም፣ የኢኮኖሚ ይዞታውም፣ ወታደራዊና የፀጥታ መዋቅሮችም፣ መገናኛ ብዙሃኑም፣ ወዘተ ወዘተ በአንድ የመንደር ልጆች ስብስብ ዙሪያ በተኮለኮለ ሃይል ፍፁም ቁጥጥር ስር ነው። ሌላው ቀርቶ የሃይማኖቱም አመራር በዚሁ ቡድን ስር ነው። ታዲያ ምን ተይዞና እንዴት ተሁኖ ነው ከዚህ ሁሉም በጄ ሁሉም በደጄ ከሆነው ቡድን ጋር ገጥሞ ማሸነፍ የሚቻለው?!

ሁኔታውን ሁሉ ልብ ብለን ካጤን ቢመረንም የምንቀበለው እውነት አለ። ተወደደም ተጠላም አሁንም የምርጫ ኮሚሽኑ፣ የምርጫውን ሂደት ሰላምና ፀጥታ የሚያስከብረው ሃይል፣ ሂደቱን የሚከታተሉና የሚዘግቡ የዜናና የመገናኛ አውታሮች፣ ገላጋይ የዳኝነት አካላት የኢሕዴግ በሆኑበት፣ የሚቻል ቢሆን የምንተነፍሰው አየርም ጭምር የኢሕአዴግ አባልና ደጋፊ ቢሆን በሚጣርበት አገር ውስጥ ተሁኖ፣ ምንም ዓይነት ከኢሕአዴግ የተለየ የፖለቲካ አጀንዳ፣ የማህበራዊና የምጣኔ ሃብት ራዕይ አንግቦ በምርጫ አሸንፎ አገር ማስተዳደር አይቻልም። አለዚያ - ይቅርና ኢሕአዴግ በ3ኛው ምርጫ ደርሶበት በነበረ ችግር ከእንቅልፉ ነቅቶና ተደናግጦ ለማጭበርጨርም ይበልጥ ራሱን አዘጋጅቶ ባለበት የአሁኑ ምርጫ ቀርቶ፣ በተዛማጅ ስሌት ዝንጉ ሆኖ በነበረባቸው ባለፉት ወቅቶች እንኳን ሊተገበር ያልቻለ ቅዠት ነው።

እዚህ ላይ አንድ ነገር መዘከር ያስፈልጋል። ባለፈው ምርጫ ዋዜማ ላይ አንዳንድ የህወሓት/ኢሕአዴግን ተፈጥሮ በሚገባ የሚያውቁ ድርጅቶች፣ ተቃዋሚዎች ኢሕአዴግ ወደ አዘጋጀው ምርጫ ዘው ብለው በመግባት የስርዓቱ "ሻማ ያገሮች" እንዳይሆኑ ባስጠነቀቁበት ወቅት ያነሷቸው መሰረታዊ ነጥቦች ነበሩ። እነዚህ ነጥቦች በምርጫው ለመሳተፍ ይቻል ዘንድ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ሲሆኑ፣ ለመጥቀስም፦

1. የምርጫ ኮሚሽኑ ከማንም ያልወገነ ወይም ከሁሉም የተውጣጣና ሁሉም ወገኖች የሚስማሙበት እንዲሆን፣
2. ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ ለተቃዋሚ ድርጅቶች የፀጥታ ዋስትና እንዲሰጥ፣
3. የምርጫውን ሂደት የሚታዘቡ ገለልተኛ አካላት እንዲጋበዙ (ፈቃድ እንዲያገኙ)፣
4. የብዙሃን መገናኛዎች (መንግስታዊው) ለሁሉም ወገን ተመጣጣኝ አገልግሎት (ዕድል) እንዲሰጡ ወዘተ የሚሉ ነበሩ።

እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢና ሊሟሉ የሚገባቸው ከመሆናቸው በላይ ለኢሕአዴግ የጠጠሩ ስለነበሩ ሳይወድ በግድ ወደ ድርድር እንዲገባ የተገደደበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ነገር ግን አንዳንድ ዛሬን እንጂ ትላንትንና ነገን ማዬት የተሳናቸው ወይም በወቅቱ ኢሕአዴግ የዴሞክራሲያዊነት ካባ በማጥለቅ ይጫወትበት በነበረው ጨዋታ

ልባቸው ያበጠ ዕቡያን አደናቃፊነት ሊገኝ የነበረውን፣ ይህ ቢያንስ ኢሕአዴግን ፍፁም ዕርቃኑን የሚያወጣ ዕድል ልንነጠቅ በቅተናል።

ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ምንም ዓይነት ብዥታ ሊኖር አይገባም። ምንም እንኳን የምርጫውን ሂደት የሚመለከት አዲስ ድንጋጌ ከተቃዋሚዎች ጋር በጋራ ተነድፏል፣ የምርጫ ኮሚሽኑም ከሁሉም ይውጣጣል ወይም ተወጣጥቷል፣ የመገናኛ ብዙሃን ለሁሉም ዕኩል አገልግሎት ይሰጣሉ … ወዘተረፈ ቢባልም፣ በገሃዱ ዓለም ያለው እውነታ ግን ከዚህ የተለየ ነው። በእርግጥ ይህን ሃቅ ላለመቀበል ምለው የደነቆሩ የመለስ አገዛዝ ታማኝ ባሪያዎች እና በተቃዋሚ ስም የሚንቀሳቀሱ ተፈጥሯዊና አገራዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው በጉርሻና በፍርፋሪ መልክ ሲቸሯቸው ብቻ የሚጣፍጧቸው፣ ሰጥቶ ለማኝ ቀለዋጮች እንዳሉ ግልጽ ነው። ትላንትም "አካሄዳችሁ ልክ አይደለም፣ የህዝብን የበላይነት ያልተቀበለና ዴሞክራሲያዊ ባህርይ ፈጽሞ የራቀው፣ በነፍጥ ብቻ የሚያስብ ፀረ-ህዝብ ቡድን ማመን አይገባም። ለምርጫው ጨዋታ የሚመቹ አሰራሮችም አልተበጁምና ተው ሲባሉ፣ እምቢኝ ብለው ጣጣ ውስጥ የከተቱን ነበሩ። ምን እንዳስገኙ ግን አይተናል። ዛሬም በዚህ ስህተት ራሳቸውን ያዘጋጁ አንድም የዋሃን፣ ሁለትም ከንቱዎች አሉ።

ለግራ ቀኙ ግልጽ መሆን ያለበትና ሁሉም የሚስማማበት ነጥብ አለ። ኢሕአዴግ የሚያካሂደው የይስሙላ ምርጫ ውብ ገጽ እንዲኖረው ይፍልጋል። ስለዚህም ጨዋታውን የሚያዳምቁለት አሰስ ገሰስ ተኮልኳዮች በጣም ይሻል። ይህንን የሚጠራጠር ሊኖር አይጠበቅም። ገገሯ ፓርቲ ብቻውን ሮጦ፣ እራሱን ቀድሞ፣ ከራሱ እጅ ሜዳሊያውን መሸለም ያፈጠጠ፣ ያገጠጠ እርቃኑን የወጣ ማጭበርበር ይሆንበታልና ማወናበጃ ወይም ማጃጃያ ሽፋን ያስፈልገዋል። በወያኔ ምስክር ወረቀት ፈቃድ የሚሰሩት የተቃዋሚ ተብዬዎች አስፈላጊነት እስከዚህ ድረስ ነው። ከዚህ በተረፈ ግን ምርጫውን ያዘጋጀውና የሚቆጣጠረው ለምርጫው የሚወዳደረውና አሸንፎ የሚወጣው ኢሕአዴግ ነው! አበቃ! እንዲያውም በግልጽ አማርኛ ለመናገር ኢሕአዴግ ምርጫውን አሸንፏል። የቀረው ወደፊት የምናዬው ለባዕዳንና ለመጽዋቾቹ የሚቀርብ ትዕይንትና ዘገባ ተውኔት ነው። በዚያ ተውኔት የሚሳተፍ ሁሉ ለዚህ ኢሕአዴግ ሊያጠልቀው ለሚፈልገው የማጭበርበሪያ ካባ የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ከማዕዱ ትርፍራፊ ለመልቀም የሚሻ ብቻ ነው።

በዚህ "በሬ ሆይ ሳሩን ዓይተህ፣ ገደሉን ሳታይ" በሚል ዜማ የተቀኘ የነቶሎ ቶሎ ቤት አካሄድ መዘዝ ደግሞ ምን እንዳስከተለ ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። የምርጫው ዋዜማ ሆያ ሆዬ፣ ሳይሆን የበርካታ ዓመታት ዕኑ ትግል የወለደው የሕዝብ ቁርጠኛ መነሳሳት ላይ ውሃ ከልብሶ፣ በትግሉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ፣ አደናቃፊዎቹም ራሳቸው የጠላታቸውን ጉልበት ስመው ምህረት እንዲለምኑ አብቅቶ አሳፍሮናል። ይህንን ተግባር ደግሞ ሁሉም ለስልት ነው የተጠቀሙበት እንዳይባል ይኸው ዛሬ የምናዬው ጉድ ገሃድ ያወጣው ነገር ነው። ትላንትና ብፁዓን ወቅዱሳን መሪዎቻችን የተባለላቸው ሰዎች (እነሱ ሆነው ሳይሆኑ ባዮቹ እንደሱ ተመኝተው) እነሱን አምኖ የተከተላቸውን ወገን ከመዝለፍ አልፈው በደሙት፣ በቆሰሉት፣ በተፈናቀሉት፣ ዘብጥያ በወረዱትና ህይወታቸውን በሰውት ላይ ቀልደው ከአረመኔ ነፍሰ-ገዳዮች ጋር፣ በእጃቸው የንፁሃን ደም ካለባቸው ጋር

ሲሞከሻሹ እና እጅ ሲጨባበጡ ከማዬት ሌላ ማስረጃ ሊቀርብ አይጠበቅም። ማንዴላነትን፣ ጋንዲነትን፣ ቴዎድሮስነትን፣ ... ያረከሱ ጎዶች ሆነው ታይቷል።

የአሁኑ ችግር ግን ይህ ያለፈው ስህተት አይደለም። ችግሩ አሁንም ይህንን ስህተት ለመድገም የመራወጡ ጉዳይ ነው። እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ህዝቡም ሆነ የህዝቡ እውነተኛ ልጆች ቆም ብለው አካሄዳቸውን መርምረው፣ ዘላቂ ጥቅማቸውን አጢነው እየተንቀሳቀሱ ለመሆናቸው ማረጋገጥ ያለባቸው። ከዚህ በመነሳት ነው የትግል ስልታችንና ግባችንን መንደፍ የሚገባን። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ሊነሱ ከሚገባቸው በርካታ ጥያቄዎች መካከል ዋነኛ ሊሆኑ የሚችሉትን (እንደ እኔ አመለካከት) የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንስቶ መልስ መስጠት የሚያስፈልግ ይሆናል፡

1. ነፃ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ተሟልተዋልን?
2. የምርጫውን ሂደት የሚመራ ነፃ አካል አለን?
3. በምርጫው ውጤት ላይ እሰጥ አገባ ቢነሳ የሚዳኝ ነፃ አካል አለን?
4. ኢሕአዴግ እውን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚያምንና የህዝብ ውሳኔን የሚያከብር ተፈጥሮ አለውን? አሜን ብሎስ ስልጣን በሰላማዊ መንገድ የሚለቅ ነውን?
5. ዓለም-አቀፉስ ማህበረሰብ ኢሕአዴግ እንደለመደው ሁሉንም ነገር በጠመንጃ ቋንቋ ማስተናገድ ቢሻው ሃይ የሚለው ይሆናልን?
6. እኛስ የህዝቡ ወገን ነን የምንል ተናግረን የምንሰማበት፣ አምርረን የምናሳስብበት አቅም አለን? ህዝቡን አደራጅተን አቅሙን ገንብተናል ወይ?
7. በእርግጥስ ኢሕአዴግን በሰላማዊ ትግል እየታገልነው ነወይ? ያስ ካልተቻለ አማራጩ ምንድነው?
8. በህዝባዊው ትግል ውስጥ ማን ምንድነው? የተቀዋሚው ጎራ ምን ያህል የተጠናከረና ግልጽ አጀንዳ አለው?

ቢያንስ ቢያንስ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት መንገዳችንን ያሳጥርልናል፣ የምንከፍለውን ዋጋም ያሳንስልን ይሆናል።

ወቅታዊ ሁኔታውን ስናጤን እላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች በሙሉ መስጠት የሚቻለው መልስ አሉታዊ ነው። ወይም አርኪ አይደለም። ቅድመ-ሁኔታዎች አልተሟሉም። ምርጫው በነፃ አካል አይመራም፣ ነፃ ገላጋይም የለም። ኢሕአዴግ የህዝብን ውሳኔ የማክበር ባህርይ የለውም። ስልጣንንም በሰላማዊ መንገድ አያስረክብም። ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም በፀረ-ሽብርተኝነት ሽርክናም ይመሃኝ ወይም በምጣኔ ሃብታዊ ትስስር ይያያዝ፣ ከጥቅሙ አንፃር ከኢሕአዴግ ጋር እንጂ ከእኛ ጋር አይደለም (ከአሥ እንባው በቀር)። እኛም ባላንባራሶች በዝተውብን ብቅ ላለው ሁሉ ሰጋጅ ሆነን፣ ፅናት ጎድሎብን፣ በሚገባ ተጠናክረን አልተገኘንምና የባዕዳንን ቀልብ በሚገባው ደረጃ የምንስብ አይደለንም። ሰላማዊ ይባል ሌላ የያዝነውን አካሄድ ጠበቅ ከማድረግ አኳያ በጣም ብዙ ይቀረናል። የተቃዋሚው ጎራም አሰስ ገሰሱ፣ መልቲውም፣ የድል አጥቢያ አርበኛውም የሚግተለተልበት ገበያ ሆኖ ጥራት ይጎድለዋል።

ታዲያ እንዴት ነው እንዲህ ተሆኖ ወደ ምርጫ የሚገባውና ለብዙሃኑ ሕዝብ የሚበጅ ውጤት ይገኛል ተብሎ የሚታሰበው?! ያለፈውስ ምርጫ የሚያስተምረን ነገር የለም?! ስንቶች ናቸው ነገር ያለቀ መስሏቸው ከምን አገባኝ ዋሻቸው ብቅ ብለው የተበሉ?! በመሰረቱ ከምርጫው የሚጠበቀው ይህን በሕዝብ የተጠላ የውሁዳን ድርጅት አሸንፎ፣ አገሪቱ ከገባችበት ሁለንተናዊ አዘቅትና ውጥረት አውጥቶ፣ ለብልፅግናና መልካም አስተዳደር ማብቃት እንጂ ድርጎ እየተቸረለት በአንድ አምባገነን ድርጅት ፍፁም ቁጥጥር ስር በሚገኝ "የተወካዮች ምክር ቤት" (የተባዮች ምክር ቤት - እያለ አንድ ወዳጄ ይሳለቅበታል) ተብዬ ጉደኛ አዳራሽ ውስጥ ተኮልኩለው ከአቶ መለስ ጋር እየተነታረኩ፣ እሳቸው የሚሉትን ምስል መስጠት መሆን የለበትም። እላይ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት ችግሮች እስካልተፈቱ ድረስ ደግሞ ከዚህ የተለየ ውጤት መጠበቅ አይቻልም።

ስለዚህ መራጭም ተመራጭም በመሆን በዚህ ሂደት ውስጥ መሳተፍ በፍፁም አይገባም። ይልቁንም ህወሓት/ኢሕአዴግ በሚነግድበት ተውኔት ባለመሳተፍ የግፈኛ አገዛዙን ዕድሜ ለማሳጠርና እርቃኑን ለማስቀረት መነሳት ይገባል። መላው የተቃውሞ ጎራና በተለይም ደግሞ በፓርላማው ተብዬ ጉድ፣ የአቶ መለስ መጫወቻ "ክቡራን" አሻንጉሊቶች ሆነው የሚገኙት የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት፣ የዚህን ፍሬ-አልባ ቧልት ጎጂነት አጢነው ምርጫውን አንሳተፍም ማለት፣ የሚሳተፉትንም መኮነን አለባቸው። እዚያ ውስጥ ተቀምጠው ለግፈኛው አገዛዝ ሽፋን እየሰጡ ለሚዲያ የፕሮፓጋንዳ ስራ ጥሬ ዕቃ ከመሆን ያለፈ ጠቃሚ ነገር አለማድረጋቸውን መረዳት ይገባቸዋል። አቶ መለስም ለአብሮ አደጎቻቸውና ለጫካ ጓዶቻቸው ለነአቶ ዓለምሰገድ ገብረአምላክ፣ ስዬ አብርሃ ወዘተ የከለከሉትን ወንበር ለነሱ የፈቀዱላቸው፣ ጨዋታውን ከማሳመር አልፈው ሌላ ችግር እንደማያመጡባቸው በመረዳት ለመሆኑ መገመት አስቸጋሪ አይሆንም። እንዲያ ባይሆንና እውነተኛ ምርጫ እንዲካሄድ ቢፈልጉማ ኖሮ ጠቅላላ ሂደቱ ዴሞክራሲያዊ እንዲሆንና ማንንም ያላገለለ በማድረግ ባመቻቹት ነበር።

በጣም ጥቅልና ግልጽ በሆነ አባባል ለማስቀመጥ ከዚህ ምርጫ የሚያተርፉት ምርጫው ከመጀመሩ በፊት ያሸነፉት የአቶ መለስ ቡድንና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ብቻ ናቸው። ስልጣን የሴት ሙሽራ፣ አቶ መለስ ደግሞ የወንድ ሙሽራ በመሆን ጋብቻቸው ተፈጥሟል፤ ተቃዋሚ ተብዬዎቹ ደግሞ አጃቢ - ያውም እነአቶ መለስ በበሉ የሚጠግቡ፣ እነአቶ መለስ በጠጡ የሚሰክሩ፣ እነአቶ መለስ በተፍነከነኩ የሚስቁ፣ እነአቶ መለስ ባስነጠሱ የሚያለቅሱ፣ ቅንጣትም ለመሰረታዊ ተቃዋሚነት ዝግጁነት የሌላቸው - ሆነው ተዘጋጅተዋል። እነአቶ መለስ በጓሮ ሳይሆን በአደባባይ ጠልፈው ላለፉት 18 ዓመታት ያገቧትንና ለሚቀጥሉትም ብዙ አስርት ዓመታት በሰማንያ ጠብቀው ሊያቆዩዋት ከወሰኗት ወይዘሮ ስልጣን ጋር ያዘጋጁትን የተውኔት ጋብቻ ለማጀብ። ገባሩ ሕዝብና እውነተኛ ተቃዋሚዎች ቀርቶ የተሓህት (ህወሓት)/ኢሕአዴግ አባላት የሆኑት እንኳን ቢሆኑ ለዋናው ቡድን ቅርበትና ጠቀሜታ ካላቸው በቀር የሚያተርፉት የረባ ነገር አይኖርም። "መበላቴ ላይቀር የመንደሬ ጅብ ይብላኝ" ዓይነት አሳፋሪ ድንቁርና ውስጥ ተዘፍቀው አዳኝ ሳይሆን ገዳይ ፍለጋ የሚዳክሩ መኖራቸውና በጭፍን ህወሓትን/ኢሕአዴግን መደገፋቸው አይካድም። ትርፋቸው ግን የአራዳ ልጆች የሚቀልዱት ዓይነት "ሽሮ ከመብላት ይልቅ በስጋ ቤት ማለፍ" ዓይነት ቀቢፀ ተስፋ ነው። ይህም ቢሆን

ለህወሓት/ኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ነው የሚቻለው። ሌላው የቀረው እበላ ባይ ሁላ እርሙን የማያወጣ ላም አለኝ በሰማይ ዓላሚ ነው።


በመሰረቱ የዚህ በሕዝብ መብት ላይ በተያዘው መቀለድ፣ ተቃዋሚዎች ብቻ ሳይሆኑ የስርዓቱ ጭፍን አጨብጫቢዎችም ሊያስቡበት ይገባል። እንዲህ እየተቀለደበትና እየተረገጠ አሜን ብሎ ለዝንተ-ዓለም የሚኖር ሕዝብም አገርም የለም። ማን ይሁን ማን ከገዳይ ጎን ተሰልፎ በመተባበሩ ከገዳይ ጋር ጣጣ ውስጥ መግባቱ እንደማይቀር መገንዘብ ብልህነት ይሆናል። ህወሓት ትግራይ ውስጥ ጦርና መሳሪያ አከማቸ አላከማቸ ቀኑ ሲደርስ ከመደቆስ አያመልጥም። ምርጫው ነፍጥ ብቻ እስከሆነ ድረስ፣ ተገፍተው ተገፍተው፣ ምርጫቸው ይህ የተሰጣቸው ብቸኛ ምርጫ ብቻ የሚሆኑ ሃይሎች መፈጠራቸውና ይህም በተግባር መፈጸሙ የማይቀር ነው። ይህ ቶሎ ባለመፈጸሙ የማይሆን የሚመስላቸው የዋሃን ወይም ተላላዎች ካሉ ልብ ይግዙ። ዛሬ በስልጣን ላይ ያለው ቡድን አባላትና በርስ በርስ የስልጣን ርኩቻው ተሽቀንጥረው ስለወረወሩ ብቻ የሕዝብ ወዳጆች ለመምሰል የሚዳዳቸው የነአቶ ስዬ - ገብሩ ቡድን አባላት አፋቸው “መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ!” እና “ከእኛ በላይ ጦርነት መስራት ላሳር!” ቢለንም ልባቸው ግን እንዲያ እንደማይል የታወቀ ነው። ከደደቢት ወደአራት ኪሎ እንደሚወስደው መንገድ ከሁሉም አቅጣጫ ሊነሳ እንደሚችል ልባቸው ያውቀዋል። ሕዝብ ተከፍቶ ሲያመርም ሺም፣ አምስት መቶ ሺም ሰራዊት፣ ሚግም፣ ሚሳኤልም እንደማያስጥል በጣሙን ያውቁታል። አቶ መለስ ፈረንጅም፣ አበሻም አያስጥልም እያሉ ቢዘባነኑበትም፣ በልባቸው ግን ሕዝብ ምንም አያመጣም ብለው እንደማያስቡ (ከልምዳቸው ያውቁታልና) በእርግጠኝነት መገመት ይቻላል። እሳቸውም ሆኑ ሌሎቹ ለሁሉም የምትሆን፣ ሁሉም አንገቱን ቀና አድርጎ የሚሄድባት አገር እስካልሆነች ድረስ ሰላም እንደማይኖር ያውቁታል።

በተቃዋሚነት ስም በስርዓቱ እግር ስር ወድቀው የሚርመጠመጡት ጉዶች ጉዳይ ግራ ቢገባም፣ የገዢው ፓርቲ አጥፊና ሕዝብን የሚያስቆጣ መስመር የመምረጥ ምክንያት ግን ለማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ በጣም ግልጽ ነው። ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ኢትዮጵያዊ ሆኖ የሚቀጥለው መግዛት እስከቻለ ድረስ ነው። እኛ “እሺ እንዳትሄዱ ግዙን እስካልናቸው ድረስ” ብቻ ነው በኢትዮጵያ መንግስትነት የሚገዙን። ይህ ዘነፍ ካለ፣ በኢሕአዴግ ስም በላያችን ላይ የሰለጠነብን ቡድን መግዛቱ መቀጠል ካልቻለ ግን የኢትዮጵያ ትዳር “እንጥስ ቢሉት ቅንጥስ” እንደሚሆን ገና ከጅምሩ ነግሮናል። እኛ እያዬን ማየት፣ እየሰማን መስማት አቅቶን፣ እራሳችንን እያታለልን እንጂ ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ ሁሌም አንግቦት የሚጓዘው አጀንዳ <u>ቢቻል በእሱ አገዛዝ ስር በኢትዮጵያ ውስጥ አብሮ መኖር፣ ካልተቻለ ተገንጥሎ የትግራይን ሪፑብሊክ ማቋቋም</u> የሚል እኮ ነው!

ይህ የሁሉም የትግራይ ተወላጆች እምነትና ፍላጎት ነው ባይባልም ስልጣንና ሰራዊቱን፣ ኢኮኖሚውን ... ጨብጦ የያዘው ወገን ዓላማ በመሆኑ ተግባር ላይ የመዋል ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው። እንደ አስመራው ቡድን ይህም ነፃነት ወይስ ባርነት ዓይነት አማራጭ አልባ አጣብቂኝ ውስጥ ከቶና አስገድዶ ዓላማውን አይተገብርም ማለት ካለፈው ስህተት አለመማር ይመስለኛል። እንዲያውም ዝግጅቱን እያጧጧፈ ለመሆኑ ምልክቶች አሉ። የተለዬ የትግራይ ብቻ ጦር ማደራጀት፣ የጦር መሳሪያ ትግራይ ውስጥ ማከማቸት፣ ትላንት ምንም ዓይነት በቂ ምክንያት ሳይኖር የዓይናቸውን ቀለም አለልወደድናቸውም ብሎ ያባረራቸውን

ኤርትራዊያንና "አምቼዎችን" ወደኢትዮጵያ ተመልሰው በእሱ ጥላ ከለላ ስር ወደጥንቱ ሁኔታቸው እንዲመለሱ እያደረገ መሆኑ የዚህ ማረጋገጫ ነው። የባህረ ነጋሽ ተወላጆቹ መመለስ ስህተት አይደለም። ስህተቱ ገዢው ቡድን እንዲመለሱ እያደረጋቸው ያለው የኢሳያስን ተቃዋሚዎች አጠናክሮ ሲያበቃ፣ የራሱን አሻንጉሊት መንግስት አስመራ ላይ በመሰዬም ድብቁን የትግራይ ትግርኝ መንግስት ለማቋቋም ካለው ዘላቂ ዓላማ ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው።

(ይህ በሰፊው የምንመለስበት ጉዳይ ቢሆንም በ http://debteraw.files.wordpress.com/2007/03/another-war-final.pdf




ወያኔ በረጅሙ የወጠነው የትግራይ-ትግሪኝ ግዛት

ከትግራይ (ቀ.1-4)፡ 1. በደቡብ ትግራይ (እንደርታ፣ ራያና አዘቦ፣ ከወሎው ራያና ቆቦም፣ አላማጣና ኮረምን ያጠቃልለ)፣ 2. ምስራቅ ትግራይ (ዓጋመ እና ሁለት አውላሎ)፣ 3. ማዕከላዊ ትግራይ (ዓድዋ፣ አክሱምና ተንቤን)፣ 4. ምዕራባዊ ትግራይ (ሽሬ፣ ከጎንደር ሑመራና ወልቃይትን ጨምሮ)

ከኤርትራ (ቁ.5-8)፡ 5. አካለ ጉዛይ (በምስራቅ በኩል ሾጠጥ ብሎ ያለውንና የሳሆ ሕዝብ የሰፈረበትን፣ በአክሱም ዘመነ-መንግስት ታዋቂ ወደብ የነበረውን አዱሊስን አጠቃሎ በማሳደግ የባህር ወደብ ለማግኘት የታቀደ)፣ 6. ሰራዬ፣ 7. ሐማሴንና 8. ከባርካ ለመውሰድ የታሰበ

የወጣውን ፅሑፍ መመልከቱ ለጊዜው በቂ ነው።)

በአጠቃላይ ኢሕአዴግ እና የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጓዙበት መንገድ አንድ አይደለም። የጉዞ አቅጣጫቸውም ግባቸውም ለየቅል ነው። ኢሕአዴግ ኢትዮጵያዊነትን አመንምኖ መግደል የመረጠ ሲሆን ሕዝቡ ደግሞ አንድነቱን መርጧል። ኢሕአዴግ አምባገነንነትን፣ ሕዝቡ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን መርጧል። ኢሕአዴግ መዝባሪነትን፣ ሕዝቡ ደግሞ ፍትሃዊ አገራዊ የሀብት ክፍፍልን መርጧል። በኢሕአዴግ እና በሕዝቡ መካከል ፍፁም የዓላማና የግብ ልዩነት አለ። እንደሁሉም ልዩነታቸው፣ በምርጫው ጉዳይ ሕዝቡና ገዢው ቡድን የማይታረቅ ልዩነት አላቸው።

ስለዚህ ሁሉም ወገን ከእነዚህ ሁለት አማራጮች አንዱን መርጦ መወገን ያለበት ይመስለኛል። ምርጫውን አስመልክቶ ምርጫችን ሁለት ብቻ ነው። የይስሙላው ምርጫ ምንም ዓይነት ሕዝባዊ አገራዊ ጠቀሜታ የሌለው መሆኑን አምነን ከሕዝቡ ጋር መወገን ወይም የወያኔ/ኢሕአዴግን ዕድሜ በማራዘም፣ የሕዝቡን ወደባሰ ድህነትና መጠነ-ሰፊ እመቃ ማምራት ለማፋጠን ከአገዛዙ ጋር አብሮ ምርጫውን ማጀብ፣ ማዳመቅ።

ተቃዋሚዎች ይህ ሳይገባቸው ቀርቷል ብሎ መገመት ትልቅ ስድብ ይሆናል። ምርጫው የሰላማዊ ትግል አካል ስለሆነ መደገፍ አለበት በማለት የተደናገሩ እንዳሉ ግን መገመት ይቻላል። በመሰረቱ ሰላማዊ ትግል ከትጥቅ ትግልም የከፋ፣ የመረረና የበለጠ ዋጋ የሚጠይቅ ስለሆነ የሚሞክረው ቆፍጣና ሲገኝ ቢደነቅ እንጂ አይኮነንም። ጉዳዩ ግን ሌላ ነው።

ሰላማዊ ትግል መብትህን አውቀህ፣ በራስ ምርጫና ትርፍ ላይ ተመርኩዘህ እንጂ ገዢው አማቂ ጠላት በሚወስንልህ ተገድበህና አሜን ብለህ እየቆነጠርክ የምታካሂደው አይደለም። ብዙ ጊዜም የእኛዎቹ በ"ውሃ ወላዋይ! ውሃ ወላዋይ..." ዜማ የተቀኙት የሰላማዊ ትግል አቀንቃኞች እየደጋገሙ ሲያነሷቸው የምንታዘበው፣ እነ ጋንዲ ተሰፍሮ የተሰጣቸውን የተቃዋሚነት ጥሬ ተቀብለው አልተቀመጡም። የመረጡትንና የጠየቁትን ነው ያደረጉት። ማንዴላም ከዚህ አትለፍና ይህን አድርግ ሲባል እምቢኝ ብሎ ወህኒ ወረደ እንጂ ምርጫውን ለምርጫቸው ግብር ሰጥቶ አላጎበደደም። እነማርቲን ሉተርኪንግም ጥቁር ከነጭ ያንሳልና አምናችሁ፣ አርፋችሁ ተቀመጡ ሲባሉ "የለም! እኩልን ነን!" በማለት ተጋፈጡ፣ መከራን ተቀበሉ እንጂ፣ ይሁን እሺ አላሉም። የኢትዮጵያ ተማሪዎችም "ዳቦ ለተራበው! ፍትህ ለሁሉም! መሬት ለአራሹ! ትምህርት ለድኻው! ..." በማለት ሲነሱ እና አርፋችሁ ተማሩ ሲባሉ እምቢ ብለው ተጋፈጡ፣ ፋኖ ተሰማራ አሉ እንጂ አልተንበረከኩም። ከቅርቦቹም ፕሮፌሰር አስራት በእስር ቤት ክህምና ተነፍገው፣ ተስፋዬ ታደሰ በወያኔ አራጆች ታርዶ፣ አሰፋ ማሩ፣ ሽብሬ ደሳለኝ ... በህወሓት/ኢሕአዴግ ነፍሰ-ገዳዮች እሩምታ ተኩስ፣ ሌሎችም ህይወታቸውን የገበሩት ሰላማዊ ትግል ሲያካሂዱ ነው። ከባህርዳር፣ ከአርባምንጭ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከጎንደር፣ ከአዋሳ፣ ከሻሸመኔ፣ ከመላው የኢትዮጵያ ከተሞችና መንደሮች እየተለቀሙ የደረሱበት የማይታወቀው የኢሕአፓም ሆነ የሌሎች ድርጅቶች አባላት ወይም ተጠርጣሪዎችም የሕዝባቸው የሰላማዊ ትግል ፈርጦች ናቸው።

እኛም የመረጥነውን ስንከለከል፣ ድምፃችን ሲታፈን፣ "የለም! አይሆንም! መብታችን፣ ደምፃችን ይከበር! ..." ማለት እንጂ ዓመታት እየቆጠርን፣ አድርጉ የተባልነውን እያደረግን በሰላም ነው እየታገልን ማለት ቀልድ ነው። አጎብዳጂነት እንደሰላማዊ ትግል ተደርጎ እየተለመደ መጥቷል። የእኛዎቹን ቀደምትም ሆነ የቅርብ ጊዜ የሰላማዊ ትግል አርበኞች በጥራዝ ነጠቅ አስተሳሰባችን ወይም ጅራፍ እራሱ መትቶ እራሱ ይጮኻል እንዲሉ በቂምኝነት ስናጣጥል እንሰተዋላለን። ከሌሎቹ ሀገሮች የሰላም ትግል አርበኞች ጋር ደግሞ ቅንጣትም ያህል የተግባር አምሳያነት ሳይኖረን ተንጠራርተን ዳግማዊ ጋንዲ፣ ዳግማዊ ማንዴላ፣ ዳግማዊ ማርቲን ሉተርኪንግ ልንባል ይከጅለናል።

የኢሕአዴግ ባህርይ ባልተለወጠበት ሁኔታ ውስጥ ሆነን (ይለወጣል የሚል እምነት የለኝም) በዴሞክራሲያዊ ምርጫ መንግስት እንቀይራለን ብለን የምናስብ ከሆነ በገሃዱ ዓለም እየኖርን አይለደም። ዛሬ ከዚህ ምርጫ ቂምነገር የምንጠብቅ ከሆነ "እባብ ሞኙን ሁለቴ ይነድፌዋል፣ አንዴ ሳያይ፣ ሁለተኛ የነደፈውን ሲያሳይ" ያሉት ቢጤ ነን።

ምርጫውን ኮንነንና አውግዘን ራሳችንን ከቧልቱ ማግለል አለብን። ይህን ሲባሉ "ሰላማዊ ትግል አታካሂዱ፣ እጅና እግራችሁን አጣጥፋችሁ ተቀመጡ ነው ወይ የምትሉን!?" የሚሉ አሉ። እየተባሉ ያሉት ግን በግልባጩ ነው። አገዛዙ ስር ስር እየተርመጠመጣችሁ፣ ለባህርይና ለምግባረ ጥፉነቱ ሽፋን እየሰጣችሁ፣ የአገዛዙን ዕድሜ በማራዘም፣፣የሕዝቡን የመከራ ዘመን አታራዝሙ ነው እየተባሉ ያሉት። ቆርጣችሁ በመነሳት፣ በምርጫ ስም የሚካሄደውን ቀልድ ተቃውማችሁ፣ የአገዛዙን ኢ-ዴሞክራሲአዊነት ባህርይ አጋልጡ። የስራ ማቆም አድማ በማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመዝጋት፣ በሰላማዊ ሰልፍ ከተሞችን የማጥለቅለቅ ስራ በመስራት፣ የገዢውን ቡድንና የአጫፋሪዎቹን ምርቶች ባለመሸመትና በእነሱ ባለመጠቀም፣ እንዲከስሩ በማድረግ፣ የሕዝብና የአገር ጠላት ለሆነ መንግስት የሚያገለግሉትን በማግለል፣ አገዛዙን ታገሉ፣ አንቀጥቅጡ፣ አንበርክኩ ነው እየተባሉ ያሉት። አለያም ደግሞ ካብ አይገባ ድንጋይ እየሆናችሁ ዴሞክራሲያዊ የሰላማዊ ትግሉን አታደናቅፉ ነው እየተባሉ ያሉት። ጥያቄው ወያኔ/ኢሕአዴግ ካሰመረላችሁ የሰላማዊ ትግል ቀይ መስመር እልፍ ብላችሁ፣ የህዝብ ድምጽ ሲሰረቅ፣ የጎንደር፣ የጋምቤላ ምድራችን ለባዕዳን በጉርሻነት ሲሰጥ፣ የዓባይ ወንዛችን መነሻ ጣና፣ የመሃል አገር ለምለሙ ምድራችን ለእስያ፣ ለአረብ ገበሬዎች ሲቸረቸር፣ ዜጎች ያለፍርድ በግፍ በጨለማ እና በወረፋ በሚተኛባቸው የዋሻ እስር ቤቶች ጭምር ሲማቀቁ አይሆንም ብላችሁ ታገሉ፣ አታግሉ ነው። ካልሆነ በሀገርና በሕዝብ ስም አትነግዱ ነው። ምንም ተባለ ምን አረመኔው ጎጠኛ አገዛዝ ሁሉንም ከአንድ ብሔር፣ በአብላጫው ደግሞ ከአንድ አውራጃ በወጡ ሰዎች ይዞ ሲያበቃ ለአዳማቂነት በሚወረውረው በርጩማ ላይ ተወዝፎ፣ ውስጠ-ርካሽ በሆነ ክቡር እንቶኔ፣ ክቡር እንቶኔ ለመባባል መሯሯጥ ሰላማዊ ትግል አይደለም፣ አይሆንምም። ይህንን ነው የምንላቸው።

እንዲያው አንዳንዴ የሚደረገውንም ማመን ያዳግታል። ለመሆኑ እነማንን ለማስመረጥ ነው የተነሳነው? የሚገርምም፣ የሚያስደንቅም፣ የሚያሳዝንም ነው። የትኞቹ ናቸው መሪዎቻችን የሚሆኑት? ከምንም በፊት ለኤርትራ ነፃነት ቆመው፣ በአገራችን ላይ ሁለገብ ጥፋት ያስከተሉትን እነአቶ ስዬ አብርሃና አቶ ገብሩ አስራት የመሳሰሉትን የናት ጡት ነካሾች?! የደርግ ዘመኑን እንተወውና ትግል ጠጠር ሲል አዛውንቱን ፕሮፌሰር አስራትን ክደው መሃል ሜዳ ላይ የጣሏቸውንና ዛሬም ጓደኞቻቸውን ክደው ከገዳይ ጋር የሚያላግጡትን፣ የንፁህንን ደም አደራ የበሉትን እንጂነር ሃይሉ ሻወልን?!

የለም! እናስተውል! አቶ ስዬም፣ አቶ ገብሩም፣ አቶ ዓለምሰገድ ገብረአምላክም፣ አቶ ተወልደም፣ ወ/ሮ አረጋሽም፣ አቶ አበበ ተክለ-ሃይማኖትም፣ አቶ ፃድቃንም፣ … ወዘተ ከአቶ መለስ እኩል ተጠያቂ ናቸው። ዛሬ በጥቅም ተከፋፍለው በሚያካሂዱት ፍትጊያ ሊዘፍቁን ቢጥሩም፣ ሁሉም ያው ናቸው። ሀሉም እኩል የኢትዮጵያን ሕዝብ ወግተዋል። በአቶ መለስ ተበልጠው ተመጠው እስኪተወረወሩበት ድረስ ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነት ነበሩ። ፀረ-ዴሞክራሲ ነበሩ።

የአረካ፣ የአርባ ጉጉ፣ የአደባባይ ኢየሱስ፣ ... እልቂት የተፈፀመውና ኤርትራ በተሓሕት/ህወሓት ጦር ተረድታና ተፈቅዶላት የተገነጠለችው አቶ ስዬ የጦር መሪ፣ አቶ ገብሩ አስራት የትግራይ ገዢ ሳሉ ነው። የአገዛዙ ባለከባድ ሚዛን፣ የፖለቲካ ቢሮ አባላት ሳሉ ነው። ይህ ሂሳብ በአግባቡ መወራረድ አለበት። ኢንጂነር ሃይሉ ሻወልም ቢሆኑ፣ ብር ቆጠራው ስራ ላይ እንጂ መብት ማስከበር ላይ አይሆንላቸውም። የሚታመኑም አይደሉም። ደርግን ካዱ፣ መኢሕድን ካዱ፣ የቅንጅት ጓደኞቻቸውን ካዱ፣ በእርሳቸው ስር ተሰልፈው የህይወት ዋጋ የከፈሉትንና ደም ያፈሰሱትን ካዱ፣ ትላንት የተመኩበትን ስደተኛ ወገናቸውን ከአንድ ሳምንት በላይ ሆያ ሆዬ አይልም ብለው ካዱት፣ በመጨረሻም የራሳቸውን አንጃ ካዱ። ራሳቸውን አለመካዳቸውን ማረጋገጫ የለንም። ሰለሌሎቹም ብዙ ሊባል ይችላል።

በአጠቃላይ ምርጫውም፣ አማራጩም ቧልት ነው። ማድረግ ያለብን ቢኖር ኢሕአዴግ ዘረፋውን ለማጠናቀቅ እንዲቻለው ጊዜ በመሸመት ላይ መሆኑ እንጂ አሁንም የታላቋ ትግራይ መርሐ-ግበሩ (ፕሮግራሙ) መሰረት እንደፀና መሆኑን ተገንዝበን፣ ራሳችንን በሁለገብ ትግል ማጠናከር ነው። በተቃዋሚው ጎራ ውስጥ ያለውን መተራመስ እጥርተን፣ ወገንና ከጠላት እየለዩን በመሰለፍ፣ ጨዋታውን ወደወያኔ ሜዳ መውሰድ አለብን - የስፖርት ጋዜጠኞችን አባባል ልዋስና። የትግሉን ጎራ ከጠባብ ብሄርተኝነትና ትምህክተኝነት አጽድተንና ለመጣው ሁሉ አርጋጅና አጎንባሽ መሆናችንን አቁመን፣ ፍሬውን ከገለባ ለይተን፣ ፖለቲካ አልወድም ቀልድን አቁመን ተደራጅተን መታገል ነው። በፓልቶክ ወግ ጥረቃ፣ በትናንሽ ጉዳይ መቧቀስ፣ በስሜትና በመሰረተ-አልባ አሉባልታ ዘመቻ መፈታት... ተጠምደን ጊዜያችንን ከማቃጠል፣ በተለይም ደግሞ የዛሬ 30 ዓመትም፣ 10 ዓመትም፣ 5 ዓመትም መልስ የተሰጣጣንባቸውን ጥያቄዎች እየመላለስን በማመንዠክ የሌለንን ጊዜ ከማጥፋት ተላቀን፣ የሚታይ፣ የሚዳሰስ ስራ መስራት አለብን።

ከሁሉም በላይ መሄጃ ስልታችንና ግባችንን አበጥረን፣ ወዳጅና ጠላትን የመለየቱ ብዥታ መጥራት አለበትና በዚህ ዙሪያ ፍፁም ግልጽ የሆነ ውይይት ማካሄድ እና ከጋራ መደምደሚያ ላይ መድረስ አለብን። ለዚህ መነሻ የሚሆኑ የውይይት ማጫሪያ ጥያቄዎች መሰንዘር ያስፈልግ ይመስለኛል። በእነዚህም ጥያቄዎች ዙሪያ ከመወራረፍ እና ከመፈራራት ተቆጥበን ግልጽ ውይይት በማካሄድ የትግሉ ጎራ ላይ ያጠላውን ብዥታ ማጥራት ይገባናል ብዬ አምናለሁ።

1. ኢትዮጵያዊነት ምንድነው? ታሪኳስ ከየት ይጀምራል? አሁንስ ምን ትመስላለች? አብረን መቀጠልስ እንችላለን ወይስ አንችልም?

2. የብሄር ፖለቲካ ምንድነው? ለኢትዮጵያስ ያስፈልጋታል?

3. የአገራችን የፖለቲካ የሃይል አሰላለፍ ምን ይመስላል? ወዳጅ ማነው? ጠላትስ? ፖለቲከኞቻችን ትላንትና እናማን ነበሩ? አሁንስ እነማን ናቸው? ዓላማቸውስ?

4. ከኢሕአዴግ ጋር መወዳደር ይገባል? ለመሆኑ ወያኔ/ኢሕአዴግ ኢትዮጵያዊ ሃይል ነው? መሰረታዊ ዓላማውስ ምንድነው?

5. የኢኮኖሚው ቁንጮ፣ የፖለቲካው ቁንጮ፣ የጦሩ ቁንጮ፣ … እነማናቸው?

6. መፃኢው የምስራቅ አፍሪካና የአገራችን ዕድል ምን ሊመስል ይችላል?

በእነዚህና መሰል ጥያቄዎች ዙሪያ ግልጽ መልስ እየተሰጣጣን፣ ብዥታችንን እያጠራን፣ ወያኔ/ኢሕአዴግን እስከሰንኮፉ በመንቀል የህዝባችንን እና የሀገራችንን ህልውና መታደግ አለብን። ሳይቀድሙን ካልቀደምናቸው፣ ዓይናችን እያዬ በሕዝብና ሀገር ላይ የሚያስከትሉት አደጋ የከፋ ነው የሚሆነው።